# 6ኛ ዙር አንደኛ የስራ ዘመን በኢፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የፕላን፣በጀትና ፋይናንስ ጉ/ቋ ኮሚቴ

# የኢፌዴሪ የገንዘብ ሚኒስቴር

# የ2014 ዓ.ም ዓመታዊ ዕቅድ ዝግጅት ላይ

# የተሰጠ ግብረ-መልስ

ህዳር / 2014

አዲስ አበባ

## የፕላን፣ በጀትና ፋይናንስ ጉ/ቋ ኮሚቴ የገንዘብ ሚኒስቴር የ2014 ዓ.ም ዓመታዊ ዕቅድ ዝግጅት ላይ የተሰጠ ግብረ-መልስ

1. መግቢያ

6ኛው ዙር አንደኛ የስራ ዘመን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሰጠውን ተልዕኮ ህግ የማውጣት፣ አስፈጻሚ አካላትን ክትትልና ቁጥጥር የማድረግ እና የውክልና ተግባራትን እንዲወጡ በህገመንግስቱ አንቀፅ 55 ከተሰጡት ተግባርና ኃላፊነት ዋና ዋናዎቹ የሚጠቀሱ ናቸው።ምክር ቤቱም የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር በብቃት ለመወጣት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎችን አደረጃጀት በምክር ቤቱ የአሰራርና የአባላት ስነ-ምግባር ደንብ ቁጥር -6/2013/እና በተሻሻለው ደንብ ቁጥር 3/2014 መሰረት አስራ አንድ ቋሚ ኮሚቴዎችን ሲያቋቋም የፕላን፣ በጀትና ፋይናንስ ጉ/ቋ/ኮሚቴ አንዱ ነው። ቋሚ ኮሚቴው ከሚያከናውናቸዉ ተግባራትም በህገ-መንግስቱ መሠረት የፌዴራል ስርዓቱን የተከተለ የክትትልና ቁጥጥር እንዲያካሂድ ተግባር እና ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

በመሆኑም ኮሚቴው የተጣለበትን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት የኢ.ፌድሪ የገንዘብ ሚኒስቴር የ2014 በጀት ዓመት የዕቅድ ዝግጅቱ ሀገራዊ 10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ ፣ የተቋሙን የ10 ዓመትና የአምስት ዓመት እቅዶች ጋር ስለመገናዘቡ፣የተቋሙን የ2013 ዓ.ም የእቅድ አፈጻጸም እና በበጀት ዓመቱ ዕቅድ ታሳቢ ያደረጋቸው የትኩረት አቅጣጫዎች፤ የእቅዱን ጥንካሬዎችና እጥረቶችን ትኩረት ሰጥቶ በመለየት ቋሚ ኮሚቴው ከዚህ እንደሚከተለው በመገምገም ግብረ-መልስ ተሰጥቷል፡፡

### 2. በጥንካሬ የተለዩ ጉዳዮች

1. የተቋሙ የእቅድ ዝግጅቱ 5 ዋና ዋና ዓላማዎች፣ 13 ስትራቴጂያዊ ግቦች፣ ስትራቴጂያዊ መለኪያዎችና ዒላማዎች መዘጋጀቱና የተግባራት አፈጻጸም ለመለካትና ለመከታተል በሚያመች ሁኔታ የተቀመጡ መሆናቸው፣

2. በበጀት ዓመቱ ሚኒስትር መ/ቤቱ የፊሲካል ፖሊሲ ዓላማዎችን ለመፈጸም የመንግሥት ገቢ በማሳደግ እና የመንግሥት ወጪ የኢኮኖሚውን ዕድገት ለሚደግፉትና ድህነትን ለመቅረፍ ለሚረዱ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች ልማት ማስፈጸሚያ

እንዲዉል ለበጀት ዓመቱ ሥራዎች በትኩረት ለመሥራት የተቃኘበት ሁኔታ ለክትትልና ቁጥጥር ተግባራት ውጤታማነትን ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ የተዘጋጀ መሆኑ፣

3.የክትትልና ግምገማ ሥርዓትን ለማጠናከር በእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት፣ የጋራ ግምገማ መድረኮች እና የመስክ ክትትልና ግምገማ ሥራዎች የተዘጋጁበት አግባቢነት ለእቅዱ አፈጻጸም ውጤታማነት የጎላ ሚና መኖሩ፣

## 3. በእጥረት የተለዩ ጉዳዮች

1. የ2014 በጀት ዓመት የባለድርሻ አካላት የቁልፍ ተገልጋዮችን ፍላጎት ያልለየ ስለመሆኑ፣

2. ከ2014 በጀት ዓመት እቅድ የሚጠበቁ ውጤቶች እቅዱ ሲዘጋጅ የBSC አሰራር ሥርዓት የተከተለ አለመሆን፣

3. እቅዱ የስትራቴጂያዊ ግቦች ማስፈጸሚያ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን የያዘ አለመሆን፣

4. የሚኒስትር መ/ቤቱ 4ቱ ፕሮግራሞች በጀት ያሉት ቢሆንም ለእያንዳንዱ ፕሮግራም የተበጀተ በጀት ለየፕሮግራሙ ተከፋፍሎ ያልተቀመጠ መሆኑና በፕሮግራም በጀት አሰራር መመሪያ መሠረት ለእያንዳንዱ ፕሮግራም በየሩብ ዓመቱ የተከፋፈለ በጀት ያለማስቀመጥ የበጀት ግልጸኝነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን እንዲሁም አፈጻጸሙን ለመከታተል አመች አለመሆን፣

5. የተቋሙ እቅድ ከዝግጅት እስከ ማጠቃለያ ያለው ሥራዎችን በምዕራፍ የተከፋፈለ የዕቅድ ዝግጅት የሌለው መሆን፣

6. የ2014 በጀት ዓመት እቅድ የድርጊት መርሀ ግብር የተዘጋጀለት ቢሆንም ለእያንዳንዱ ግቦች የተቀመጡ ዒላማዎች አንዳንዱ ለየሩብ ዓመቱ ያልተከፋፈለ መሆን፣ለአብነት፡-የ2014 በጀት ዓመት እቅድ ዒላማዎች፣ግቦችና መለኪያዎች (አባሪ ሠንጠራዥ)ይመልከቱ።

7. በድርጊት መርሀ ግብር መሰረት ለአንዳንድ ግቦች የ2013 በጀት ዓመት አፈጻጸም ተገምግሞ ለ2014 በጀት ዓመት እቅድ መነሻ ዒላማዎች ያልተቀመጠላቸው መሆኑ፣

8. ለሚኒስትር መ/ቤቱ ተጠሪ የሆኑ ተቋማትን ዕቅድ አፈጻጸም ለመከታተልና ለመደገፍ በሚያስችል መልኩ ቁልፍ ተግባራት ተለይተው በሚስቴር መ/ቤቱ ዕቅድ ውስጥ አለመካተት (ከመንግሥት ልማት ድርጅቶች አስተዳደር በስተቀር)፣

## 4. ትኩረት የሚደረግባቸው ጉዳዮች

1. በ2014 በጀት ዓመት እንዲከናወኑ በዕቅድ የተያዙ የመንግሥት ሜጋ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ወጪ ቆጣቢና ውጤታማ እንዲሆኑ በመንግሥት ፕሮጀክቶች አስተዳደርና አመራር ሥርዓት መሰረት ስራ ላይ መዋላቸውን ትኩረት ሰጥቶ ድጋፋዊ ክትትል ማድረግ፣

2. የመንግሥት አገልግሎት ዘርፍን ለማሻሻል የተዘጋጀው ፍኖተ-ካርታው በእቅድ እየተመራ ተግባራዊ ለማድረግ በትኩረት መስራት፣

3. የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም መሰረት ያደረገው በማክሮ ኢኮኖሚ፣ በመዋቅራዊ እና በሴክተር ዋና ዋና ምሳሶዎች ላይ ትኩረት ሰጥተው መስራት፣

4. የበጀት ጉድለትን ለመሸፈን መንግሥት የሚከተለውን ፖሊሲ በገበያ ስርዓት የሚመራ የወለድ ምጣኔና የገንዘብ አመዳደብ ለመተግበር የበጀት ጉድለት መሸፈኛ አማራጮችን በማስፋት የገንዘብ ገበያውን ለማጠናከር በቀጣይነት ትኩረት ሰጥቶ መስራት

5. የፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን ክትትልና ግምገማ ስርዓት በማጠናከር አገራዊ የልማት እቅዶች እንዲሳኩ በትኩረት ማከናወን፣

6. ለፌዴራል ባለባጀት መ/ቤቶችና ለመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች የጋራ መጠቀሚያ እቃዎች /የማዕቀፍ ግዥዎች፣አገራዊና ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸውን እቃዎች የግዥ ሥርዓትን በተከተለ ወቅቱና ጥራቱን የተጠበቀ ግዥዎችን እንዲከናወኑ ሚኒስትር መ/ቤቱ አፈጻጸሙን በትኩረት ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣

7. የመንግስት ንብረት አስተዳደር ደንብና መመሪያ መሰረት በማድረግ በዓመቱ የንበረት ቆጠራ በማድረግ በክዋኔ ኦዲት አሰራር መሰረት የክዋኔ ኦዲት ግኝቱን ለሚመለከተው በማቅረብ ተጠያቂነትን እንዲሰፍን በክትትልና ቁጥጥር ማረጋገጥ፣

## 5. ማጠቃለያ

የሚኒስትር መ/ቤቱ የ2014 በጀት ዓመት የዕቅድ ዝግጅት ከሀገራዊ 10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ፣ የተቋሙ የ10 ዓመትና የአምስት ዓመት እቅዶችና ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በህግ ከተሰጡት ኃላፊነቶችና ተግባራት ጋር የተገናዘበና የተቋሙን የ2013 ዓ.ም የእቅድ አፈጻጸም ጉድለቶችን ለይቶ ያወጣ በመሆኑ ያለፉት ዓመታት ጠንካራ አፈጻጸሞች የበለጠ በማጎልበትና ጉድለቶችን እጥረቶችን በማረም እና ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን መሰረት በማድረግ  መፈጸም ከተቻለ ሊያሰራ የሚችልና ውጤት የሚጠበቅበት ነው፡፡